የመ/ቁ.18342

*ታህሣሥ* 17 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች**፡- የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን

**መልስ ሰጭዎች**፡- 1ኛ- አቶ ብርሃኑ ህሩይ
2ኛ- አቶ ከበደ ገ/ማርያም

*ስለማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ - የማኅበራዊ ዋስትና ባልስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 38/1988 አንቀጽ 11/1/ ፡- ስለፍርድ ቤቶች ስልጣን -የፍትሐ ብሄር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 4*

የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማኅበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኂላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ስለሰጠና ውሳኔውንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስላደናው የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሣኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሸሯል፡፡

1. በህግ ተለይተው በአስተዳራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፡፡
2. የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስራ ነገር ስልጣን የላቸውም፡፡



የሰ/መ/ቁ. 18342

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ተገኔ ጌታነህ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ነገረፈጁ አቶ ፈርተውሃል ኃ/ጊዮርጊስ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ አቶ ብርሃኑ ሕሩይ ቀረበ
2ኛ/ አቶ ከበደ ገ/ማርያም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የሆኑት የአሁኑ ተጠሪዎች በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረን ስናገለግል በቆየንባቸው ዓመታት ለጡረታ አበል እየተባለ ከደመወዛችን ከመቶ አራት፣ ከአሠሪው መሥሪያ ቤት ደግሞ በመቶ ስድስት እየተቀነሰ ለማህበራዊ ዋብትና ባለሥልጣን ገቢ ተደርጓል ያሉትን ገንዘብ የሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ወደነበረበት እንዲመልስ፣ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በበኩሉ ያለአግባብ ከከሣሾች ሂሣብ ወጪ በማድረግ ለትምህርት ቤቱ የሰጠውን ገንዘብ ወደነበረበት ሂሣብ ተመላሽ እንዲያደርግ በሚል የሰጠውን ውሣኔ ከፍተኛው ፍ/ቤት ትክክል ነው ብሎ በማጽናቱ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በዚህ ጉዳይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸው ምክንያቶች የአሁኑ ተጠሪዎች ይህንኑ ከጡረታ አበል ጋር የተያያዘውን ገንዘብ ጉዳይ በሚመለከት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ጥያቄ አቅርበው መሥሪያ ቤቱ በሕጉ መሠረት አይቶ ከወሰነ በኋላ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አመልክተው የመጨረሻ ውሣኔ ሰጥቶበታል ጉባዔው በአዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 11(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ስለሆነ ከዚህ በኋላ በዚሁ ጉዳይ ለፍ/ቤት ክሥ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሠረት ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሎ መወሰን ነበረበት፡፡ ከጡረታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተነሣውን ጥያቄ መደበኛ ፍ/ቤት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም፡፡ የህንን ጉዳይ በየደረጃው የተመለከቱት ፍ/ቤቶች ሕጉን በአግባቡ ሣይተረጉሙ ቀርተዋል በሚል የቀረቡ ናቸው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ የሚጣሩ የሕግ ነጥቦች ያሉት ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻም ለአሁኑ ተጠሪዎች ተልኮ ግንቦት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የመልስ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል፡፡

በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ አመልካች ያለአግባብ ከእኛ ሂሣብ አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ በሚመለከት የጡረታ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንም ሆነ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ክሥ አቅርበን በሥማችን ውሣኔ ስለመስጠቱ የሚያስረዳ ማሥረጃ አላቀረበም፡፡ የአገልግሎት ዘመናችን ተቀንሶብናል ወይም ያለአግባብ ዕድሜአችን ለጡረታ ሣይደርስ በጡረታ እንድንገለል ተደርጓል በሚል ያቀረብነው ክስ ስለሌለ በጡረታ ሕጉ መሠረት የሚታይ ጉዳይ የለም፡፡ አመልካች አላገባብ ከሂሣባችን አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ ተቀብሎ ወደነበረበት ሂሣብ እንዲያስገባ በሚል የቀረበውን ክሥ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት አመልካቹ መሥሪያ ቤትን ጠይቆ የወሰደው ገንዘብ አላገባብ መሆኑን አምኖ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት መልሶ ገቢ ስላደረገ አመልካች አልፈጽምም የሚልበት ምክንያት የለም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ችሎቱም የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ይፈፀምልን ያሉትን ጉዳይ ፍርድ ቤት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡ በአዲስ መልክ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5 ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚፈጽማቸውን ተግባሮች እና የተሰጠውን ሥልጣን የሚዘረዝር ሲሆን በዚህ አንቀጽ ሥር ከታቀፉት ንዑስ አንቀጾች መካከል በንዑስ አንቀጽ 8 ላይ የተመለከተው ሲታይ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን አግባብ ባላቸው ሕጐች መሠረት በሚቀርቡ የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን በግልጽ ያረጋግጣል፡፡ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በዚሁ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም በሚመለከት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው በአዋጁ አንቀጽ 11 ላይ ሥልጣን ለተሰጠው ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርቡትን ይግባኞች መርምሮ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ነው፡፡ በሕጉ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በአንድ የማህበራዊ



ዋስትና ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ነው ከተባለ ከዚህ በኋላ በይግባኝ ደረጃም ሆነ በክሥ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የሚሄድበት መንገድ የለም ማለት ነው፡፡ በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍ/ቤት ሊያስተናግድም ሆነ አከራክሮ ውሣኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንዳንድ የመንግሥት አስተዳደር አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጡት ሕጐች መጠበቅና መከበር ይኖርባቸዋል፡፡ የዳኝነት አካሉ ሥልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጐም ሥራው በሕግ ማቀፍ የሚመራ ነው፡፡ ስለዚህ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ሁሉ ፍርድ ቤት አይቶ ከመወሰን ሊገደብ አይችልም የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት የለውም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.4 ላይ በፍርድ ቤቶች እንደተገለፀው በሌላ ሕግ በግልጽ ከታገዱ በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን የላቸውም፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካችን ሊከሱ የቻሉበት ምክንያት እና ባቀረቡት ክስ ይፈፀምልን በሚል ያነሱት ጥያቄ ከማህበራዊ ዋስትና ጉዳይ ጋራ ተያያዥነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ሲመረመር በመጀመሪያ በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ ቢቆዩባቸው አመታት ለጡረታ መዋጮ እየተባለ ከእያንዳንዳቸው ደመወዝ በወር በመቶ አራት፣ ከአሠሪው መሥሪያ ቤት ደግሞ በመቶ ስድስት እየተዋጣ በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በየሥማቸው በተከፈተ ሂሣብ ገቢ ሲደረግ የቆየው ገንዘብ በኋላ ወደተዛወሩበት የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት መተላለፉን ገልፀዋል፡፡

ተጠሪዎች የአሁኑ አመልካች የጡረታ መዋጮውን ወደሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ያስተላለፈው አላገባብ ነው ይበሉ እንጅ በክሣቸው ላይ ከገለፁት ፍሬ ነገር እንደሚታየው ከጥር ወር 1989 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እንዲገለሉ ተደርጓል፡፡ ወደ ሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት እንዲተላለፍ ተደርጓል የሚሉት ትምህርት ሚኒስቴር ሲሰሩ በነበረበት ወቅት የተዋጣው የጡረታ መዋጮ ወደ ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እንዲመለስ የሚጠይቁትም ተመልሶ በእነርሱ ሥም በተከፈተ ሂሣብ እንዲቀመጥ ለማድረግ ብቻ ሣይሆን ይኸው ታስቦ በጡረታ አበላቸው ላይ እንዲጨመር ለማድረግ ወይም በሕጉ መሠረት ይገባናል የሚሉትን መብት ለማስከበር እንጅ ለሌላ ጉዳይ ለማመቻቸት አይደለም፡፡ የምናነሣው የማህበራዊ ዋስትና መብትም ሆነ ጥቅም የለም የሚሉ ከሆነ ደግሞ የጡረታ መዋጮው ቀደም ሲል በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሥማቸው ተከፍቶ ወደነበረው ሂሣብ እንዲመለስ የሚጠይቁበት ምክንያት አይኖርም፡፡ የጡረታ መዋጮም በቀጥታ ከማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም ጋራ ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡ ተጠሪዎች ወደሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ተላልፏል የሚሉት የጡረታ መዋጮ ወደ ማህበራዊ ዋስትና

ባለሥልጣን እንዲመለስ ተደርጐ በሕጉ መሠረት የሚገባን የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም አለ ካሉ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5(8) መሠረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ጥያቄአቸውን አቅርበው ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ አለባቸው፡፡ ተጠሪዎች ትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ በቆዩባቸው አመታት ተዋጥቷል የሚሉት የጡረታ መዋጮ እንዲተላለፍ ከተደረገበት የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ወደማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ካዝና እንዲመለስ መጠየቁ ብቻ በሕጉ ትርጉም የለውም፡፡ ወደ ሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ተላልፋል የተባለው የጡረታ መዋጮ እንዴት ይሆናል? በጡረታ አበል ሊታሰብላቸው ይገባል አይገባም የሚለውን ጥያቄ በሕጉ የመወሰን ሥልጣን ያለው ራሱ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና በይግባኝ ደረጃ የሚያየው ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ እንጅ ፍርድ ቤት አይደለም፡፡

በሌላም በኩል የአሁኑ አመልካች በክርክሩ ላይ እንደገለፀው ይኼው ጉዳይ ቀደም ሲል ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ቀርቦ እስከ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ ደርሶ ታይቶ ውሣኔ ከተሰጠበት እንደገና የሚታይበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በሕጉ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ በመሆኑ ያበቃለት ጉዳይ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤት በሥረ ነገሩ ላይ የመዳኘት ሥልጣን የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ይህንን ጉዳይ በማስመልከት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 2384 ታህሣሥ 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔም ሆነ ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በክርክሩ ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ



መ/ቁ.14699

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሀይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** የኢንጂነር ወርቁ መኮንን የአመልካች ወራሾች

**ተጠሪ፡-** የቦሌ ክ/ከተማ ገቢዎች መምሪያ

*ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሕጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ - የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29*

አመልካች ገቢ ለመፍጠር ወጪ ያደረጉት ገንዘብ በወጪነት ሳይያዝ ግብር እንዲከፍሉበት የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ገንዘብ በወጪነት እንዲያዝላቸው የጠየቀ ሲሆን የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም ወጪ ለመውጣቱ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ በወጪነት ሊያዝላቸው ይገባል በማለት ሲወስን ጉዳዮን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ውሳኔ ያፀናው ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን የቀረቡት ማስረጃች በግብር ሕጉ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛ ሰነዶች ስላልሆኑ በወጭነት ሊያዙ ስለማይገባ ግብር ይከፈልባቸው በማለት ውሳኔ በመሥጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ዉሳኔ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29 «ትክክለኛ» ሰነዶች እንዲቀርቡ የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ወጪች በቀጥታ ገቢን ለመፈጠር ስለመውጣታቸው በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ እና ግብር ከፋዩ ሃሰተኛ ሰነድ በማቅረብ የግብር ግዴታውን እንዳይሸሽ ለመቆጣጠር እንጂ የሰነዶችን አዘገጃጀት ሥነ-ሥርዓት መሟላት አለመሟላት ለመቆጣጠር አይደለም፡፡
2. ሰነዶቹ መ/ቤቱ እንዲሟሉ የሚፈልጋቸው ሥርዓቶች ባያማሉ እንኳ ወጪ ለመውጣቱ ሊያረጋግጡ የሚችሉ በቂ ሁኔታችን እስካሳዩ ድረስ ተቀባይነት የማያገኙበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡